# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

የካቲት29/1999

## ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን

## የኢትዮጵያ ሴቶች ትግል ፍትህዊ ነው

የኢትዮጵያ ሴቶች ለሀገራቸውና ለመብታቸው ሲታገሉና መስዋዕትነት ሲከፍሉ የቆዩ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የመብታቸው ባለቤት ናቸው ማለት አይቻልም:: በየካቲት 66 በተለይ ሴቶች ለመብታቸው ሊታገሉ በፖለቲካው መድረክ ላይ ብቅ ማለታቸውና ቀጥለውም መደራጀታቸው እንደ አንድ ጉልህ ምዕራፍ የተመዘገበ ሲሆን የሕዝብን ድል ነጥቆ ስልጣን የያዘውንም ወታደራዊ አገዛዝ በገጠርም በከተማም ታግለው መስዋዕትነትን ከፍለዋል:: የዓለም አቀፍ ሴቶች ቀን በሀገራችን እንዲከበርም የሆነው ለሴቶች መብት በተደረገው ትግል መሆኑ የሚታወስ ነው::

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአሁኑ ጊዜ የሴቶችን መብት ረግጦ ለይስሙላ ግን መብታቸውን አከብራለሁ እያለ በተለይ ወጣት ሴቶችን ለመከራና በደል ዳርጎ ይገኛል:: በገጠር ያሉት ሴቶች በተለይ እየደረሰባቸው ያለው ጭቆናና ብዝበዛ አሰቃቂ ነው:: በከተሞች ወጣት ሴቶች ለሴተኛ አዳሪነትና አልፎም ለቀሳፊ በሽታ መዳረጋቸው ከጤና ጠንቅነቱ በተጨማሪ እያደረሰው ያለውን ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት በሀዘንና በምሬት እየተመለከትነው ያለ ክስተት ነው:: በርካታ ሴቶች ወደ መካከለኛው ምስራቅ ለዘመናዊ ባርነትም ይላካሉ:: የሀገሪቷን ህግ በተፃረረ መልክ እየተካሄደ ያለውም ህፃናትን ለባዕድ በጉዲፈቻ መልክ መሸጥ አገዛዙ የሚያስጠይቅና የሚያስወግዝ ነው:: ሴቶች በሀይል እየተደፈሩ፤ ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ እየተዳሩ፤ አካላቸው ላይ ጉዳት እየተፈፀመ፤ የትምህርት ዕድል እየተነፈጋቸው፤ በሥራ ቦታም ልዩነት እየተደረገባቸው ወዘተ በአጠቃላይ የበደል ሰለባና መብት አልባ ሆነው ይገኛሉ::

ሴቶች የህብረተሰቡ ግማሽና ከዚያም በላይ አካል ናቸው:: ሴቶች ባለመብት ሆነው በሁሉም መስክ በእኩልነት የማይሳተፉበት ህብረተሰብ ከዴሞክራሲ ሆነ ከዕድገት አንፃር ከባድ ችግርና ጉድለት ያለው ነው:: የሴቶች መብት መከበሩንም በሚመለከት የሴቶች ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡን በአጠቃላይ ዴሞክራሲ ፈላጊውን በሞላ የሚመለከት ነው:: ኢሕአፓ የሴቶችን መብት በማክበርና ለዚሁም ከሴቶች ጎን ሆኖ በመታገል አቋሙን በገቢር አስመስክሯል:: የሴቶችን መደራጀት በመደገፍና በማገዝ፤ ሴቶችን በድርጅቱ አሰልፎ በማታገል የኢትዮጵያ ሴቶች ለሀገራቸውና ለመብታቸው ታግለው አኩሪ ታሪክን እንዲያስመዘግቡ አስተዋፅዖ አድርጓል::

ዛሬም ቢሆን--በተለይም በአሁኑ ወቅት--በሚካሄደው ሀገር አድን ሁለገብ ትግል ሴቶች በትግሉ ገብተው የሚጠበቅባቸውን ሚና ይወጡ ዘንድ ጥሪ ያደርጋል:: ከድላይ እስከ ፅጌ÷ ጀሚላና መስከረም÷ ስመኝና እጅጋየሁ÷ እነ ትርሲት÷ ፈትለና አበራሽ÷ ብዙ ሺ ሴቶች በኢሕአፓነት ታግለው አርዓያ ሆነዋል:: የኢትዮጵያ ሴቶች ትግል ፍትሃዊ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ሴቶች ራሳቸው ለመብታቸው የታገሉና የሚታገሉም መሆናቸውን አስመስክረዋል::

የኢትዮጵያ ሴቶች ፍትህዊ ትግል ድልን ይቀዳጃል!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
USA
Tel: (202)-291-4217
Fax: (202)-291-7645
E-mail: ESPIC@aol.com

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
FRANCE

Website: http://www.EPRP.com

EPRP
Postbus 1253
1000 BG Amsterdam
HOLLAND